# MCPS QUICKNOTES

**ሴፐቴምበር 4/2019**

**የ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ታላቅ አጀማመር**
የ 2019-2020 የትምህርት ዓመት በታላቅ ድምቀት የተጀመረው ማክሰኞ ሴፐቴምበር 3 የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከበፊት ይልቅ ቁጥራቸው ከፍተኛ ለሆኑ ተማሪዎች በሩን ክፍት በማድረግ ነው። በዚህ ዓመት በዲስትሪክቱ 207 ትምህርት ቤቶች ከ164,000 በላይ ተማሪዎች ይከታተላሉ፣ ከ2018-2019 የትምህርት ዓመት የተማሪዎች ቁጥር በ1,500 ይበልጣል።

ዲስትሪክቱ በተጨማሪ 21 አዳዲስ ርእሰመምህራንን (ወይም ለትምህርት ቤቶቻቸው አዲስ የሆኑ) የተቀበለ ሲሆን፣ እነዚህም ርእሰመምህራን አዳዲስ ተማሪዎቻቸውን እና ቤተሰቦችን ለመገናኘት በጋለ ስሜት ተዘጋጅተው ነበር። አንዳንዶቹ ከእነዚህ ርእሰመምህራን የትምህርት ቤታቸው ማህበረሰብ እንዲያውቀዉ የሚፈልጉትን ለ MCPS QuickNotes ስለ ራሳቸው አስደሳች ቁምነገሮችን ወይም አስደሳች እውነታ አካፍለዋል፦

**የአንደኛ ደረጃ (ኤሌሜንታሪ) ት/ቤቶች**

Laura Swerdzewski, Acting Principal, Beverly Farms Elementary School ሎራ ስወርደዘውስኪ፣ በቨርሊ ፋርምስ ኤለመንተሪ ት/ቤት ተጠባባቂ ርእሰመምህር፣
ያደግሁት ከ Long Island በስተምሥራቅ መጨረሻ ዌስትሃምፕተን ቢች/Westhampton Beach ሲሆን በእጆቼ መጻህፍት ይዤ የእግር ጣቶቼን አሸዋ ዉስጥ ሳደርግ በጣም ደስተኛ ነኝ። የትምህርት ዓመት ተጀምሮ አዲስ ጅማሮዎችን ለማየት እና ለሁሉም ተማሪዎቻችን የልቀት ባህላችንን ለመቀጠል ከበቨርሊ ፋርምስ/Beverly Farms ማህበረሰብ ጋር የመሥራት እድልን በጋለ ስሜት እጠብቃለሁ!

Greg Baron, DuFief Elementary School ግሬግ ባሮን፣ ዱፊፍ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
በሜሪላንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ/Maryland and with MCPS የማስተማር ሙያ ከመጀመሬ በፊት በሦስት የተለያዩ ስቴቶች (ካሊፎርንያ፣ ፍሎሪዳ፣ እና ሜሪላንድ) እና ሁለት የተለያዩ አገሮች (ዩ.ኤስ.ኤ እና ኢንግላንድ) በአስተማሪነት የመሥራት እድል ነበረኝ።

Robert Obstgarten, Greencastle Elementary School ሮበርት ኦብስትግርተን፣ ግሪንካስል ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
ባለቤቴ እና እኔ ሁለታችንም የ MCPS መምህራን ስንሆን፣ የ7 ዓመት እድሜ ያለው ወንድ ልጅ እና የ3 ዓመት እድሜ ሴት ልጅ ወላጆች በመሆናችን ኩራት ይሰማናል። ተማሪዎቻችንን በሙሉ ምርጥ እራሳቸውን እንዲሆኑ ለመርዳት የግሪንካስል/Greencastle ማህበረሰብን ለማገልገል በመታደሌ ክብር ይሰማኛል።

Stephanie Dinga, Goshen Elementary School ስተፊኒ ዲንጋ፣ ጎሸን ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
የኮሌጅ ተግባሬን የጀመርኩት ዳንስን ሜጀር አድርጌ ስለነበረ 26 ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ በካምፓኒዎች እደንስ ነበረ።

Rosario Velasquez, Jackson Road Elementary School ሮዛሪዮ ቫለስኲይዝ፣ ጃክሰን ሮድ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
እኔ የተወለድኩት ፔሩ/Peru ሲሆን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ-United States የመጣሁት የ 8 ዓመት ልጅ ሆኜ ነው። በቤተሰቤ ውስጥ እኔ የመጀመሪያው አስተማሪ ነኝ።

Jessica Palladino, Rolling Terrace Elementary School ጄሲካ ፓለዲኖ፣ ሮሊንግ ተሬስ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
የኔ የ MCPS የስር ሐረግ ጥልቅ ነው! የእኔ የወንድ አያት እና እናቴ ከብሌር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Blair High School ተመርቀዋል እና እኔ ከስፕሪንግብሩክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Springbrook High School ተመርቄአለሁ።

Gary Rand, Sligo Creek Elementary School ጆሪ ራንድ፣ ስላይጎ ክሪክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ/Montgomery County Public Schools የተወሰኑ አስደሳች ትዝታዎችን፣ እና ተማሪ፣ አትሌት፣ እና መሪ የመሆን እድሎችን ሰጥቶኛል። በስላይጎ ክሪክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት/Sligo Creek Elementary School ርእሰመምህር ሆኜ መልሼ ለመስጠት እድል ስላገኘሁ ክብር ይሰማኛል።

Yolanda Allen, Snowden Farm Elementary School ዮላንዳ አለን፣ ስኖውደን ፋርም ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
በኤለመንተሪ፣ በመካከለኛ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሦስቱም ደረጃዎች አስተምሬአለሁ። እኔ "Matlock and Law & Order" የመሣሠሉ የተከታታይ ድራማዎች ትልቅ ደጋፊ ነኝ።

Karin Wade, Travilah Elementary School ከሪን ዋዴ፣ ትራቪለህ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
ጉዞ ማድረግ፣የምህዳር ዳሰሳ እና ስለ ሌሎች ባህሎች እና ታሪክ መማር እወዳለሁ።

Daman Harris, Wheaton Woods Elementary School ደማን ሃሪስ፣ ዊተን ውድስ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት
የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ 'Heads Up!' የተሰኘ የልጆች የቴሌቪዥን ጥያቄዎች "TV quiz show for kids" ላይ እወዳደር ነበር። አሁን፣ የኔን ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና የሥራ ባልደረቦችን በየእለቱ መጠየቅ እችላለሁ!

## የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች

Aaron Shin, Parkland Middle School አሮን ሺን፣ ፓርክላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
እኔ በዊሊያም ቴይለር ፔጅ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት (William Tyler Page ES)፣ በብሪግስ ቼኒ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Briggs Chaney MS)፣ እና በፔይንት ብራንች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Paint Branch HS) በመማር ከ MCPS የተመረቅሁ ነኝ። እንደዚሁ በፓርክላንድ/Parkland ለዘጠኝ ዓመት ሠርቻለሁ እና ወደዚህ ድንቅ ማህበረሰብ ትምህርት ቤት በመመለሴ ደስተኛ ነኝ።

Matthew Nipper, Acting Principal, Redland Middle School ማቲው ናይፐር፣ ተጠባባቂ ርእሰመምህር፣ ሬድላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
አስደናቂ ከሆነው የሬድላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Redland MS ማህበረሰብ ጋር ለመሥራት የጋለ ስሜት አለኝ! በሬድላንድ/Redland፣ ለተማሪዎቻችን በሙሉ "#BeTheOne for ALL" ለመሆን ቁርጠኞች ነን!

## ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

Christine Handy, Albert Einstein High School ክሪስቲን ሃንዲይ፣ አልበርት አይንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
ለብሄራዊ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰመምህራን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ፕሬዚደንት ሆኜ በመመረጤ ምክንያት ለአንድ ዓመት በስራ ፈቃድ/leave of absence ወደተለየሁት ሥራ መመለሴ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰመምህርነት 20ኛ ዓመቴን ለመጀመር ጓጉቻለሁ።

Kevin Yates, Damascus High School ከቪን ያተስ፣ ደማስከስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
ኮሌጅ እያለሁ፣ አካለስንኩልነት ላለባቸው ሰዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ እና ግንዛቤ ለማስጨበጥ በዩ.ኤስ በብስክሌት ተዘዋውሬአለሁ። ከባለቤቴ እና እድሜአቸው 20፣ 19፣ 16 የሆነ ሦስት ልጆቻችን ጋር ከቤት ውጪ ጊዜ ማሣለፍ ደስ ይለኛል።

Mark Carothers, Poolesville High School ማርክ ካሮዘርስ፣ ፖልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
Leukemia እና Lymphoma ላለባቸው ማህበረሰብ $30,000 ለማሰባሰብ ሲባል 11 ማራቶኖችን ሮጫለሁ እና ግማሽ "Ironman" ሁነት አጠናቅቄአለሁ።

**ለሁሉም ተማሪዎች ሠላማዊና ደስ የሚያሰኝ ት/ቤት መፍጠር**
አዲሱ የትምህርት ዓመት ተጀምሯል እናም የሠላምና የፀጥታ/ደህንነት ጉዳይ በብዙዎቻችሁ አእምሮ እንደሚመላለስ እናውቃለን። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና ዓላማ እንደ ት/ቤት ስርአት ሁሉንም ተማሪዎች ለወደፊታቸው መሻሻል ለማብቃት እያዘጋጀቸው ቢሆንም፣ ተማሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና በትም /ቤት ተቀባይነት ካላገኙ ይህ ሊደረስበት አይቻልም።

የአውቶቡስ እና የህንፃ ደህንነትና ሠላምን ጨምሮ፣ የልጅ ማጎሳቆል፣ ማስጨነቅ/ወከባ እና ራስን መግደል መከላከል፣ እና የአካባቢ ደህንነትን በመንከባከብ ሠላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ለማቅረብ MCPS ሁለገብ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

ዲስትሪክቱ የተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች መካከል ከዚህ በታች ያሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡-

**ስለ ደህንነት ግንባታ**

- ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተሻሻለ የት/ቤት የድንገተኛ/የአስቸኳይ ጊዜ እቅዶች [የበለጠ ግንዛቤ ይውሰዱ]
- በትምህርት ቤት አስቸኳይ-ድንገተኛ ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ እርዳታ ለማድረግ የሚችሉ በተጠንቀቅ የሚገኝ ቡድን በሥፍራው አለ።
- ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት፣ የእሳት አደጋ መከላከል አገልግሎት፣ እና ሌላ የካውንቲ ኤጀንሲዎች ጋር በአደጋ/ድንገተኛ/አስቸኳይ ጊዜ ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ የሚያስችል ትብብር [MOU ያንብቡ]
- በሁሉም ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ተቋማት የሚገኙበት ቦታዎች ላይ የትምህርት ቤት ደህንነት ግምገማዎች ይካሄዳሉ
- ስለእሳት እና ድንገተኛ-አስቸኳይ ከባድ የአየር ሁኔታዎች  የደህንነት ጥበቃ ልምምዶች ይሰጣሉ
- ጥቃት በሚደርስበት ወቅት ለሚፈጠር ድንገተኛ አደጋ ጥራት ያለው-የተሻሻለ የዝግጁነት ስልጠና [የበለጠ ግንዛቤ ያግኙ]
- በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሪሶርስ ኦፊሰር ይኖራል [የበለጠ ያንብቡ]
- በጠቅላላ በካውንቲው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን የሚረዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ለዓላማቸው የቆሙ የMCPS ሰኩሪቲ/የጥበቃ ሠራተኞች
- በት/ቤቶች ላይ መቆጣጠሪያ ያላቸው የመግቢያ በር ሲስተም
- ለትምህርት ቤቶች የደህንነት ጥበቃ ጥይት መከላከያ ሰደርያ/ቨስቲቡለስ/vestibules ማሠራጨት

- የብሔራዊ እና የስቴት የጾታዊ ጥቃት ፈጻሚዎች የመረጃ ቋት-ዳታቤዝ ቢኖርም በትምህርት ቤቶች የጎብኚ ማኔጅመንት ስርዓት ወደ ት/ቤት የሚመጡ ሁሉንም ጎብኚዎች ለማጣራት
- ስለ ት/ቤት ሠላም እና ደህንነት አጠቃላይ ሪፖርት የ 2018 ሪፖርት እና የሥራ እቅድ ያንብቡ
- በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በሚድል ስኩል በሙሉ የደህንነት ካሜራዎች፣ በኤለመንተሪ ት/ቤቶችም ካሜራዎች እየተጨመሩ ናቸው
- ለትምህርት ቤቶች የሪሶርስ ኦፊሰሮች እና የሰኩሪቲ ሠራተኞች አስፈላጊ የሆነ ስልጠና መስጠት
- ሠላም እና ደህንነትን ለመገንባት የሁሉንም የሥራ ባልደረቦች ንቃት እና ትኩረት መስጠት

**ከትምህርት ቤት ሠዓት-በኋላ ክትትል/ቁጥጥር**

- የስፖርት እና ከትምህርት ቤት-ሠአት በኋላ የሚኖር እንቅስቃሴን በንቃት የመከታተል እና የመቆጣጠር ፕላኖች
- ሴፕቴምበት 2019፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የስቴት ዓቃቤ ህግ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ከትምህርት-ሠዓት በኋላ ስለሚደረጉት የደህንነት ቁጥጥር ሁኔታ የውጫዊ አካል ግምገማ ይፋ ይደረጋል

**የተማሪ ጤንነት እና ደህንነት**

- "Be Well 365" የተሰኘ አጠቃላይ የማህበራዊ-ስሜት ክህሎትን መገንባት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ይበልጥ ያንብቡ
- vaping ስለማጨስ አደገኛነት ሪሶርሶች (Link/ሊንክ)
- ትምህርት ቤት የሚገኙ የጤንነት-ደህና ቁመና ማእከሎች
- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የት/ቤት ማህበረሰብ ጤና ነርስ ወይም የትምህርት ቤት ጤና ክፍል ቴክኒሻን ይበልጥ ግንዛቤ ያግኙ
- ለሁሉም የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች ራስን ስለማጥፋት የመከላከል ስልጠና
- ስለ አእምሮ ጤንነት ቀውስ፣ ማስጨነቅ/ማገባጠር፣ ስለ ረብሻ እና ሌሎችም ስጋቶችን  በምስጢር ሪፖርት ለማድረግ ክፍት መስመር (ይበልጥ ይወቁ)
- *BTheOne* ከ "Montgomery County, Every Mind and Family Services, Inc ጋር በመተባበር ስለ አእምሮ ጤንነት ዘመቻ (ስለ ዘመቻው ይበልጥ ያንብቡ)
- የማስፈራራት ስነምግባር ምርመራን በሚመለከት የሠራተኞች ስልጠና
- በሁሉም ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ሁለገብ የጤና ሥርዓት ትምህርት/ከሪኩለም
- ለተማሪዎች የአእምሮ ጤንነትና ቀውስ ሪሶርሶች እና እርዳታ ይበልጥ ያንብቡ
- ራስን መግደል ስለመከላከል እና ጣልቃ ገብነት ለሁሉም ሠራተኞች ግዴታ የሆነ ስልጠና
- ራስን የመግደል ስጋት ሪፖርት ማድረግያ የማያቋርጥ ሂደት ይበልጥ ያንብቡ
- የትምህርት ተነሣሽነት አገናኝ መረቦች/Linkages ይበልጥ ግንዛቤ ያግኙ
- ከሱሰኝነት ለሚመለሱ ተማሪዎች የተኃድሶ አካደሚክ ፕሮግራም ይበልጥ ይገንዘቡ
- ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የእፅ ተጠቃሚነት መመርመሪያ እና ህክምና ሪሶርሶችን ይመልከቱ
- ለተማሪዎች የፍትኃዊ ተሀድሶ ፕሮግራሞች ይበልጥ ይገንዘቡ
- ለትምህርት ባለሙያዎች አስፈላጊነት ያለው/Mandatory የብቃት ባህልን ስለማዳበር ስልጠና መስጠት

**የእግረኛ ተጓዥ ደህንነት**

- የእግረኞች ደህንነት ሪሶርሶች ይበልጥ ይገንዘቡ
- ስለ እርግረኞች ደህንነት የህዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ-ወደ ትምህርት ቤት መድረስ እሽቅድምድም አይደለም “Getting to School is Not a Race” የተሰኘውን ቪድዮ ይመልከቱ
- የእግረኞችን እና ብስክሌተኞችን ደህንነት ለማጎልበት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር ጋር መተባበር ቪድዮ ይመልከቱ
- ስለ እግረኞች ደህንነት የሚሰጥ ትምህርት በጤና ትምህርት ላይ ተካቷል

እና ሌላም ብዙ። [እዚህ ክሊክ ያድርጉ ](#)ከዋና የደህንነት ኦፊሰር ስለ ደህንነት ያስተላለፉትን መልክት ለማንበብ

**"Youth Cruiser SmarTrip Card" በመጠቀም ተማሪዎች በነፃ መጓዝ ይችላሉ**

እድሜአቸው 18 ወይም ከዚያ በታች የሆኑ የ MCPS ተማሪዎች "Youth Cruiser SmarTrip Card" በመጠቀም ሁልጊዜም በ "Ride On" አውቶቡስ በነፃ መጓዝ ይችላሉ። ለተማሪዎች ይሄ ተጨማሪ የመጓጓዣ ዘዴ ሊገኝ የቻለው ምስጋና ይግባቸውና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራስንፖርቴሽን ዲፓርትመንት ትብብር ነው።

ይህ አሠራር በተማሪዎቻችን ላይ የሚፈጥረውን ተፅእኖ MCPS ለማወቅ እንዲረዳ፣ የእርስዎን አስተዋጽኦ እንጠይቃለን። [እባክዎ ይህንን አጭር ](#)ዳሰሳ ይሙሉ ነፃ የ"Ride On" መጓጓዣ አገልግሎት ለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት የእርስዎን የትራንስፖርት ውሳኔ እንዴት ሊነካ እንደሚችል።

Youth Cruiser SmarTrip Card ነፃ ካርድ እንዴት እንደሚገኝ ይበልጥ መረጃ ለማግኘት [ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ ](#)።

**የቅዳሜ ት/ቤት ተማሪዎችን ስኬታማ እንዲሆኑ ያግዛል።**

የጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ (George B. Thomas, Sr. Learning Academy) የ 2019-2020 የቅዳሜ ት/ቤት Saturday School ቅዳሜ ሴፕቴምበር 21 ይጀምራል። የቅዳሜ ት/ቤት የMCPS ተማሪዎች የዋነኛ አካዴሚያዊ ርእሶች ልቀታቸውን ለማበልፀግ የሚያግዛቸው ባለ-ኣነስተኛ-ዋጋ የቱተር እና ሜንቶር ፕሮግራሞች የሚከናወንበት ስድስተኛዉን የትምህርት ቀን የሚያቀርብ ፕሮግራም ነው። ተጨማሪ ኣካዴሚያዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በ Montgomery County ዙሪያ ከሚገኙት 12 ቦታዎች ኣንዱ ላይ ፕሮግራሞችን መከታተል ይችላሉ። ትምህርቶች የሚጀምሩት **ቅዳሜ፣ ሴፐት. 21** ነው በሜይ ወርም ያልቃል። የምዝገባ ዋጋ ነፃ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ/Free and Reduced-price Meals (FARMS) ለሚቀበሉ $40 ሲሆን FARMS ለማይቀበሉ ደግሞ $85 ነው።

[ጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ/George B. Thomas, Sr. Learning Academy](#)

**ሴፕቴምበር 15 የሚካሄደው "FutureFest" የተሰኘ የቤተሰብ ፌስቲቫል ኢያምልጥዎት**

ደስታ፣ ቀልድ፣ ጫወታ ላይ ይሳተፉ [FutureFest](#)፣ እሑድ ሴፕቴምበር 15 የሚካሄድ ነፃ የቤተሰብ ፌስቲቫል Veterans Plaza and the Silver Spring Civic Center።

ሁነቱ የሚካሄድበት ሠዓት ከእኩለቀን እስከ 5 p.m. ሲሆን ልጆች የተባበረ ኃይላቸውን ተጠቅመው ወደፊትን እንዲፈጥሩ እድል ይሰጣቸዋል! ይህ ሁነት ደስታ፣ ቀልድ፣ ጫወታ ሁሉም አሉት፡ እውነተኛ ደስታ። እውነተኛ-ትክክለኛ መሣሪያዎች። እውነተኛ-ትክክለኛ የመጪው ዘመን ክህሎቶች። የፌስቲቫሉ ፍንጮች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- KID City፡- የወደፊት ከተማ ግንባታ ሥራ ላይ ይሳተፉ! ኃይል በሚያመነጩ መሣሪያዎች ቤት መገንባት፣ በ"3D-printed bolts" በመጠቀም ቅርፃ ቅርጾችን መፍጠር፣ በሴንሰር የሚንቀሳቀስ የመንገድ/ጎዳናዎች ብርሀን አብሪ እና ሌሎችንም መገንባት።
- ባህላዊ መስቀልኛ መንገዶች፡- ለማህበረሰባችን ቅርጽ የሰጡ በእጅ የሚሠሩ ስራዎች፣ በህብረት የስነጥበብ ምስረታዎች፣ ሙዚቃ እና የዳንስ ትርኢቶች ይዳሰሳሉ።

- የፈጠራ ኤክስፖ፡- ዓለማችንን የሚቀይሩ ፈጠራዎችን ይቃኙ። ስለወደፊት ጠፈር እና ዳሰሳ፣ ከተሞች እና መጓጓዣ/ትራንስፖርቴሽን፣ ጤና እና ደህንነት፣ ምግብ እና በዘላቂነት መኖር እና የሚበልጥ በውልብታ መመልከት።

FutureFest KID Museum ከሞንትጎመሪ ካውንቲ እና ፈንድ ፎር ሞንትጎመሪ/Montgomery County and the Fund for Montgomery ጋር በመተባበር ይ